# ፖሊሲ

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ**
**BOARD OF EDUCATION OF MONTGOMERY COUNTY**

**ተዛማጅ ደንቦች፡-** ACA, ACF, ACF-RA, ACH, ACI, ACI-RA, BBB, GCA-RA, KBA, KBA-RA, JHF, JHF-RA ድርድር የተደረገባቸው ስምምነቶች/Negotiated Agreements

**ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፡-** የሰው ሀብት ልማት ቢሮ
Office of the Human Resources and Development

## የሰራተኛ የስነምግባር ጉድለት ምርመራ

### A. ዓላማ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች የተፈጸሙ የስነምግባር ጉድለቶችን ምርመራ ስለማካሄድ መርሆችን ለማቋቋም

### B. አቋም

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ሁሉም ሰራተኞች በቦርድ ፖሊሲዎች እና ዋና እሴቶች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች እና *በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ* (MCPS) (*ከዚህ በኋላ*) "MCPS *ህጎች/ደንቦች የተሰኘ*) *የሰራተኛ የስነ ምግባር ደንብ* ላይ የተቀመጡትን ህጎች እና የስነምግባር ደረጃዎችን እንዲያከብሩ ይጠበቃል።

2. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) –

   a. ከቦርድ ፖሊሲ ACA፣ *አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት፣ እና የባህል ብቃት የሠፈነበት ደንብ ጋር* በማጣጣም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) ህጎች በፍትሃዊነት፣ በእኩልነት እና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ይተገብራል፤ እና

   b. ተመሳሳይ ጉዳዮችን ወጥነት ያለው አካሄድና አፈጻፀም በመጠቀም የእነዚህን ሕጎች (ከዚህ በኋላ "*ሥነ ምግባር የጎደለው ተግባር*") ጥሰትን ሙያዊ በሆነ መንገድ ያጣራል።

3. ማንኛውም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውስጥ ምርመራ የማድረግ ግብ የጥፋተኝነት ተጠርጣሪነትን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ ሲሆን ዋና ዋና እውነታዎችን በሚያረጋግጥ ጥልቅ እና ተጨባጭ የምርመራ ሂደት፣ በማስረጃ ላይ የተመሠረቱ ክፍተቶችን መፍትሔ ለማሻት መረጃ ይሰበስባል፣እናም ጉድለቶችን ለማሻሻል ወይም አለመግባባቶችን ለመፍታት እንደዚህ ያሉ ማስረጃዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ።

### C. የአተገባበር ስልቶች

የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት –

1. ከዚህ እንደሚከተለው የሰራተኛን የስነምግባር ጉድለት የሚመለከቱ ምርመራዎችን ለመቀበል፣ ለመገምገም፣ ለመከታተል፣ እና ለማስወገድ የጉዳዩን አፈጻጸም እና አስተዳደራዊ ሂደት ያቋቁማል፣

   a. ሪፖርት አቅራቢ ራሱ(ሷ)ን በመግለፅም ሆነ ማንነቱ(ቷ) ሳይገለጽ በሠራተኛ የስነምግባር ጉድለት ላይ ስሞታ/ክስ ሲቀርብ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውጭ የሚተዳደር ሚስጥራዊ የሆነ ለሕዝብ ክፍት የስልክ መስመር እንዲኖር ማድረግ፤

   b. ራሱ(ሷ)ን በመግለፅ ወይም በምስጢር የሚቀርቡ ሪፖርቶችን ወደ ሶፍትዌር ድራይቭ የሚመዘግብ የጉዳይ መከታተያ ስርዓት ማብጀት፣ እና

   c. በምስጢር የተጠቆሙ ሁሉንም ቅሬታዎች በመከታተል ቅሬታ አቅራቢ እራሱ(ሷ)ን በሚገልጽበት አሰራር መሠረት አስፈላጊ መረጃዎች ላይ የተሞረኮዘ ምርመራ ማድረግ።

2. ስለ ምርመራዎች አፈጻጸም እና የሰነዶች አያያዝ ግልጽ መመሪያዎችን ማዘጋጀት እና እነዚህን መመሪያዎች በየዓመቱ ክለሳና ማሻሻያ ማድረግ።

3. ተዛማጅ የፌደራል እና የስቴት ህግን፣ የቦርድ ፖሊሲዎችን፣ እና በድርድር የተከናወኑ ስምምነቶችን፣ የትምህርት ቤቶች እና የዲስትሪክት ኦፕሬሽኖችን፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦችን ያካተተ በሥራ ክፍል አመራር እና መርማሪዎች መካከል የተመጣጠነ እውቀት ፖርትፎሊዮ በማዘጋጀት ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የምርመራ ክፍል ሰራተኞች ጥበቃ የቅጥር፣ የቆይታ ጊዜ፣ የአፈጻጸም ግምገማ፣ የፍትህ ሂደት፣ እና የሜሪላንድ ሠርተፊኬት መስፈርቶችን ጨምሮ የሰራተኞችን መብቶች እና ጥቅማጥቅሞች በተመለከተ የሚጠበቁትን መስፈርቶች ማስቀመጥ።

4. መርማሪዎች መከተል ያለባቸውን ፕሮቶኮሎች ማዘጋጀት፦

   a. ማንኛውንም የጥቅም ግጭት (በተጨባጭ የሆነ፣የመሆን አዝማሚያ ያለው፣ ወይም ይሆናል ተብሎ የታሰበ) ወይም ከተጠርጣሪው(ዋ)፣ ከተጠቂው(ዋ) ወይም ከምሥክር ጋር ያለን ግንኙነት ወዲያውኑ ግልፅ ማድረግ፤ ወይም በተጠርጣሪው(ዋ)፣ በተጠቂው(ዋ) ወይም በምስክር ላይ በምርመራው ተጨባጭነት ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር የሚችል ከሆነ፣ ወይም ሌሎች ያህንን ተጨባጭነት እንዲጠራጠሩ የሚያደርግ ከሆነ በፍጥነት ግልፅ ማድረግ፣

   b. በኤጀንሲ የሚካሄዱ ምርመራዎች ላይ ጣልቃ የመግባት ወይም አደጋ ላይ የመጣልን ማንኛውንም ሁኔታ ለማስወገድ ከሚመለከታቸው ውጫዊ ኤጀንሲዎች (ለምሳሌ፦ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች፣ የሜሪላንድ ስቴት ዓቃቤ ህግ ቢሮ እና/ወይም የህጻናት ጥበቃ አገልግሎት ወይም የልዩ ተጠቂዎች ክፍል) ጋር መተባበር/ማስተባበር።

   c. ለሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ ግንዛቤ ማስጨበጥ፤ (ለምሳሌ፦ ለደረሰ ጥቃት ምላሽ ሰጭ ክፍል፣ ለቅሬታ አቅራቢው(ዋ)፣ እና ማናቸውም ምስክርነት ለሚሰጡ) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በምርመራ ውስጥ ለሚሳተፉት በሙሉ ከማናቸውም የበቀል እርምጃ ጥበቃ የሚደረግላቸው መሆኑን፤ እና

   d. የምርመራውን ትክክለኛነት መጠበቅ-

      i) ሁሉንም ማስረጃዎች እና ሰነዶችን መጠበቅ፣

ii) የምስጢራዊነት መስፈርቶችን በሙሉ ማክበር እና

iii) የተቋቋሙ የአፈጻፀም ሂደቶችን በታማኝነት መተግበር።

## D. የሚጠበቁ ውጤቶች

1. የሰራተኞች ስነምግባር በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ህጎች ላይ የተቀመጡትን ከፍተኛ የስነምግባር እና የተጠያቂነት ደረጃዎች ማሟላት አለበት።

2. ማንኛውም የሰራተኛ የስነምግባር ጉድለት ተጠርጣሪነት ሙሉ በሙሉ ሙያዊ የአፈጻፀም ሂደቶችን በመከተል በታማኝነት ምርመራ መደረግ አለበት።

3. ምርመራ አድራጊ(ዎቹ) ላይ ሌሎች ትክክለኛነታቸውን እንዳይጠራጠሩ ብቃት ያላቸው፣ የማያዳሉ፣ እና (በእርግጠኝነት የሆነ፣ ሊሆን ከሚችል፣ ወይም ይሆናል ተብሎ ከሚታሰብ) ከማንኛውም አይነት የጥቅም ግጭት የፀዱ መሆን አለባቸው።

4. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መርማሪዎች ቁልፍ የሆኑ እውነታዎችን በመመስረት በማስረጃዎች ላይ ክፍተቶችን በመሙላት እና በማስረጃዎች ላይ የተከሰቱ ጉድለቶችን ወይም አለመመጣጠንን በመፍታት ረገድ ጥልቅ እና ተጨባጭ ምርመራ ማከናወን ይጠበቅባቸዋል።

## E. ግምገማና ሪፖርት

ይህ ፖሊሲ በትምህርት ቦርድ የፖሊሲ ግምገማ መርህ መሠረት በየጊዜው ክለሳ ይደረግበታል።

የፖሊሲው ታሪክ፦ አዲስ ፖሊሲ በውሳኔ ቁጥር...ጸድቋል።